ማ.ኢ.ክ.ፖ.ጥ.ም.ኢ.

CERPSRI

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የፖሊስ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት

Central Ethiopia Region Policy Study and Research Institute

# የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል
# የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት
# አጠቃላይ ተቋማዊ ገፅታ

# ተልዕኮ

ተመራጭ የፖሊሲ አቅጣጫዎችና ስትራተጂዎች መንደፍ የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን የሚያመላክቱ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድ ለክልሉ መንግስትና ለአካባቢው ሁለንተናዊ ልማት ድጋፍ ማድረግ

# ራዕይ

መንግስት ልማትና መልካም አስተዳደር ለማረጋገጥ በያዘው የረጅም ጊዜ ዕቅድ በእውነታ ላይ የተመሰረተ መረጃ፣ ሳይንሳዊ መርሆ የተከተሉ የፖሊሲ አቅጣጫዎች፣ ስትራተጂዎች መንደፍ የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን በማመንጨት የሚያቀርብ ተመራጭና ተአማኒ የጥናትና ምርምር ተቋም መሆን፣

# 1 የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ምስረታና አደረጃጀት

በአዲስ በተደራጀው የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የተፋጠነ ልማትና ሁለንተናዊ ዕድገት ማረጋገጥ የሚያስችሉ የተለያዩ ፖሊሲዎች፤ ስትራተጂዎች፤ አዋጆች፤ እና ደንቦች ፀድቀው ስራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል። እነዚህ በክልሉ የተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር እየተተገበሩ ያሉ የፖሊሲና የህግ ማዕቀፎች አፈፃፀም ውጤታማነት ደረጃ ከተቋም ተቋም እንዲሁም ከማስፈፀምና ከመፈፀም አቅም አንፃር ልዩነት ሊፈጥር እንደሚችል የሚታመን ነው። በመሆኑም በክልሉ የፖሊሲና ህግ ማዕቀፎች ትግበራ በታለመለትና በታሰበው መንገድ እንዳይተገበር እንቅፋት የሆኑ ተግዳሮቶች በአግባቡ ተለይተው የመፍትሄ አማራጮች ሊቀመጥ ይገባል። በዚህም አግባብ የማ/ኢ/ክ/የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት በተለያዩ የፖሊሲ ጉዳዮችና የህግ ማዕቀፎች አተገባበር የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች ጥናትና ምርምሮችን በማድረግም ሆነ በማስተባበር የመፍትሔ አማራጮችን የሚያቀርብ ተቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በአዲሱ ክልል መልሶ እንዲደራጅ የተደረገ ተቋም ነው።

በክልሉ የሚነደፉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና የሚሰጡ ውሳኔዎች በጥናት ለመደገፍ የረጅም ጊዜ የጥናትና የምርምር ዕቅድ በመንደፍ ሙያዊ

ድጋፍ የሚሰጥ ተቋም መደራጀት ለክልሉም ሆነ ለሀገሪቱ ልማት ዕድገት መፋጠን የሚኖረው ድርሻ ከፍተኛ ከመሆኑ ባሻገር የሕዝቦችን አብሮነትና የጋራ እሴቶቻቸውን ለማጎልበት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የክልሉ ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ሊቋቋም ችሏል። ኢንስቲትዩቱ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የመስተዳደር ምክር ቤት የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 199/2015 አንቀጽ 39 ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት ከተደራጁ የክልል ተቋማት አንዱ ነው። በመሆኑም ከኢንስቲትዩቱ ልዩ ባህሪይ ጋር የሚመጥኑ የምርምር ሥራዎችን ማካሄድና ማስተባበር የሚያስችል የተሻለ አቅም፣ ዝግጁነት የተላበሰና ፍላጎት ያለው ከፍተኛ የባለሙያዎች ቡድን ወደ ተቋሙ ለመሳብና ለማቆየት፤

እና ባጠቃላይ የክልሉን ሁለንተናዊ ልማት መደገፍና ማፋጠን የሚያስችል ምሁራዊ አቅም ለመፍጠር ታስቦ የተቋቋመ ኢንስቲትዩት ነው።

ኢንስቲትዩቱ በዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሆኖ ለዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪ የሆኑ እና የኢንስቲትዩቱን ዘርፎች በተደራጀ አግባብ የሚመሩ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች አሉት። የክልሉ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት በአራት ዘርፎችና በድጋፍ ሰጪ የተደራጀ ሲሆን ዋና ፅህፈት ቤቱ ሆሳዕና ከተማ ላይ ይገኛል። ኢንስቲትዩቱ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ለመወጣት የሚያስችለው አደረጃጀትና የሰው ሃይል በአዲስ ተጠንቶለት ወደ ሥራ የገባ ተቋም ነው። ተቋማዊ ለውጡ የተደረገው የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት በማድረግ ሲሆን፤ ይህም ዘርፎችን/ቡድኖችን

በመለየት ተቋማዊ አደረጃጀቱ እንዲሻሻል አድርጓል። በመሆኑም፤ 35 የተከለሱ የድጋፍ ሰጪ የስራ መደቦች፤ እና 32 የተከለሱ የተመራማሪ የስራ መደቦች በመያዝ፤ ለተቋሙ በአጠቃላይ 67 የተከለሱ የስራ መደቦች ፀድቀዋል።

ኢንስቲትዩቱ በራሱ አደረጃጀትና የሰው ሃይል ከሚሰራቸው የጥናትና ምርምር እንዲሁም ተያያዥ ሥራዎች ባሻገር ከፍተኛ ተመራማሪዎች ካላቸው የከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት እና ሌሎች ለጥናትና ምርመምር አቅም መፍጠር የሚያስችሉ ግብአቶች ካሉአቸው ተቋማትና ታዋቂ ተመራማሪ ምሁራን ጋር ግንኙነት በመፍጠር የሚሰራ ይሆናል።

## የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የፖሊሲና ስትራቴጂ ሐሳቦችን ያመነጫል፤ በፖሊሲ ጉዳዮች የክልሉን መንግሥት ያማክራል፤
2. በፖሊሲዎችና ስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ ወቅታዊና ጥልቀት ያለው ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤ የመፍትሔ ሐሳብ ያመነጫል፤
3. የክልሉን ፖሊሲና ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ ፍላጎት፣ ዕውቀትና ዝግጁነት ያላቸውን ተመራማሪዎችን ይለያል፣ ያስተባብራል፤ እንደ አስፈላጊነቱ ከዩኒቨርሲቲዎችና ሌሎች የምርምር ተቋማት ጋር በመተባበር የፖሊሲና ስትራቴጂ ጥናትና ምርምር ያካሄዳል፤የፀደቀ

የምርምር ውጤት ያሳትማል፤ ያሰራጫል፤

4. የመንግሥት ተልዕኮ ለማሳካት የመንግሥት ድጋፍና አመራር ለማጠናከር የሚያግዝ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተወዳዳሪነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ተቋማዊ ግንባታ አስመልክቶ መነሻ ሐሳብ ያመነጫል፤ ጥናት ያካሂዳል፤የጥናቱ ግኝት ለሚመለከተው የመንግስት አካል ቀርቦ ተግባራዊ እንዲሆን የበኩሉን ጥረት ያደርጋል፤

5. የተለያዩ ሴሚናሮችን ወርክ ሾፖችንና የጉባኤ መድረኮችን ያዘጋጃል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበርም የአጫጭር ሥልጣናዎችን እያዘጋጀ ይሰጣል፤

6. በክልሉ ከሚገኙ ተቋማት ጋር በመተባበር የተቋማትን የማስፈፀም አቅም ለማጎልበት የሚረዱ ጥናትና ምርምር ስራዎችን ያካሂዳል፤

7. ለፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ጠቃሚ የሆኑ ግብዓቶች ካሉአቸው ተቋማትና ታዋቂ ምሁራን ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፤

8. ከውጪ ሀገሮች የጥናትና የምርምር ተቋማት ጋር በመሆን ምርጥ ተሞክሮዎችን ይለዋወጣል፤ ይለያል፣ ይቀምራል፣ ያስፋፋል፣ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤ የጥናትና ምርምር ውጤት ያሰራጫል፤

9. ሌሎች ለኢንስቲትዩቱ ዓላማ መሳካት ጠቀሜታ ያላቸውን ተግባራት ያከናውናል

# 2 የኢንስቲትዩቱ ምርምር ዘርፎች ሁኔታ

የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት አደረጃጀት፣ መዋቅርና የሥራ ዝርዝር በኢንስቲትዩቱ ማቋቋሚያ ደንብ ላይ እንደሰፈረው ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነታቸው ለዋና ዳይሬክተሩ የሆኑና በምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚመሩ አራት ዘርፎች አሉት። አራቱም ዘርፎች እያንዳንዳቸው በስራቸው የጥናትና ምርምር ቡድኖችን ያቀፉ ሲሆን ስለ ቡድኖቹ መሰረታዊ ነጥቦች እንደሚከተለው ቀርቧል።

## i. የኢኮኖሚ ፖሊሲ ጥናት ዘርፍ

ይህ ዘርፍ በክልል ደረጃ ከኢኮኖሚ ዘርፍ ጋር በተያያዘ ጥናትና ምርምር ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን መለየት፣ በስራ ላይ እንዲውሉ የተደረጉ የዘርፉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና አሰራሮችን አተገባበር በመዳሰስ የጥናት ርዕሰ ጉዳዮችን መለየት፣ ከመንግስት የኢኮኖሚ ተቋማት ጋር የተያያዙ አዳዲስ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና አሰራሮችን ማጥናት የሚያስችል የጥናት ርዕሰ ጉዳዮችን ማቅረብ፣ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን በማከናወን አዳዲስ

እውቀቶችን ለማመንጨት እና በሥራ ላይ ያሉትን ፖሊሲዎችንና አሰራሮችን ለማጠናከርና ለማሻሻል የሚያስችሉ ችግር ፈቺ የፖሊሲ ምክረ ሃሳቦችን ማፍለቅ፣ የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ መቀመር፣

ሳይንሳዊ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር መጽሔት ዝግጅት ላይ መሳተፍ፣ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ጥናትና ምርምር የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፣ የዘርፉን የጥናትና ምርምር የክትትልና ድጋፍ ሥራዎችን የሚያከናውን ነው።

ዘርፉ የተሰጠውን ተግባር በቅልጥፍናና በውጤታማነት ለማከናወን ያስችለው ዘንድ በአምስት የጥናትና ምርምር ቡድኖች የተደራጀ መዋቅር ተበጅቶለታል። እያንዳንዱ የጥናት ቡድን ደግሞ በስሩ ጀማሪ ተመራማሪ፣ ረዳት ተመራማሪ፣ ተመራማሪ፣ ከፍተኛ ተመራማሪ፤ እና መሪ ተመራማሪ በሚል የተለዩ የተመራማሪ ሙያዊ ደረጃዎች የሚደራጁ ናቸው።

በዚህ ዘርፍ የሚገኙ የጥናትና ምርምር ቡድኖች የሚከተሉት ናቸው፡-

i. የንግድ ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ቡድን
ii. የአካባቢና አየር ንብረት ለውጥ ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ቡድን
iii. የግብርና ማዘመንና ገጠር ልማት ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ቡድን
iv. የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ቡድን
v. የከተማና መሰረተ ልማት ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ቡድን

## ii. የማህበራዊ ፖሊሲ ጥናት ዘርፍ

ይህ ዘርፍ በክልል ደረጃ ከማህበራዊ ዘርፍ ጋር በተያያዘ ጥናትና ምርምር ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን መለየት፣ በስራ ላይ እንዲውሉ የተደረጉ የዘርፉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና አሰራሮችን አተገባበር በመዳሰስ የጥናት ርዕሰ ጉዳዮችን መለየት፣ ከመንግስት የማህበራዊ ተቋማት ጋር የተያያዙ አዳዲስ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና አሰራሮችን ማጥናት የሚያስችል የጥናት ርዕሰ ጉዳዮችን ማቅረብ፣

የማህበራዊ ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን በማከናወን አዳዲስ እውቀቶችን ለማመንጨት እና በሥራ ላይ ያሉትን ፖሊሲዎችንና አሰራሮችን ለማጠናከርና ለማሻሻል የሚያስችሉ ችግር ፈቺ የፖሊሲ ምክረ ሃሳቦችን ማፍለቅ፣ ጠቃሚ የሆኑ የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ መቀመር፣ ሳይንሳዊ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር መጽሔት ዝግጅት ላይ መሳተፍ፣ የማህበራዊ ፖሊሲ ጥናትና ምርምር የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፣ የዘርፉን የጥናትና ምርምር የክትትልና ድጋፍ ሥራዎችን የሚያከናውን ነው።

ዘርፉ የተሰጠውን ተግባር በቅልጥፍናና በውጤታማነት ለማከናወን ያስችለው ዘንድ በሦስት የጥናትና ምርምር ቡድኖች እንዲደራጅ መዋቅር ተበጅቶለታል። እያንዳንዱ የጥናት ቡድን ደግሞ በስሩ ጀማሪ ተመራማሪ፣ ረዳት ተመራማሪ፣ ተመራማሪ፣ ከፍተኛ ተመራማሪ፤ እና መሪ ተመራማሪ በሚል የተመራማሪ ደረጃዎች

ተለይቶ የተደራጁ ናቸው።

የዚህ ዘርፍ የምርምር ቡድኖች የሚከተሉት ናቸው፡-

i. የድህነት ትንተናና የማህበራዊ ደህንነት ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ቡድን

ii. የሰው ሃብት ልማትና የሥራ ስምሪት ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ቡድን

iii. የስርዓተ ፆታ፣ የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ቡድን፤

## iii. የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ፖሊሲ ጥናት ዘርፍ

ይህ ዘርፍ በክልል ደረጃ ከዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ዘርፍ ጋር በተያያዘ ጥናትና ምርምር ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን መለየት፣ በስራ ላይ እንዲውሉ የተደረጉ የዘርፉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና አሰራሮችን አተገባበር በመዳሰስ የጥናት ርዕሰ ጉዳዮችን መለየት፣ ከመንግስት የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ተቋማት ጋር የተያያዙ አዳዲስ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና አሰራሮችን ማጥናት የሚያስችል የጥናት ርዕሰ ጉዳዮችን ማቅረብ፣

የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን በማከናወን አዳዲስ እውቀቶችን ለማመንጨት እና በሥራ ላይ ያሉትን ፖሊሲዎችንና አሰራሮችን ለማጠናከርና ለማሻሻል የሚያስችሉ ችግር ፈቺ የፖሊሲ ምክረ ሃሳቦችን ማፍለቅ፣ ጠቃሚ የሆኑ የሌሎች አገሮችን

ተሞክሮ መቀመር፣ ሳይንሳዊ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር መጽሔት ዝግጅት ላይ መሳተፍ፣ የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ፖሊሲ ጥናትና ምርምር የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፣ የዘርፉን የጥናትና ምርምር የክትትልና ድጋፍ ሥራዎችን የሚያከናውን ነው።

ዘርፉ በተመሳሳይ የተሰጠውን ተግባር በቅልጥፍናና በውጤታማነት ለማከናወን ያስችለው ዘንድ በሦስት የጥናትና ምርምር ቡድኖች እንዲደራጅ መዋቅር ተበጅቶለታል። እያንዳንዱ የጥናት ቡድን ደግሞ በስሩ ጀማሪ ተመራማሪ፣ ረዳት ተመራማሪ፣ ተመራማሪ፣ ከፍተኛ ተመራማሪ እና መሪ ተመራማሪ የሚባሉ የተመራማሪ ደረጃዎች ባሉአቸው ባለሙያዎች የሚደራጁ ናቸው። የዚህ ዘርፍ ቡድኖች የሚከተሉት ናቸው፡-

i. የፌዴራሊዝም ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ቡድን

ii. የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ቡድን

iii. የተቋማት ልማት ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ቡድን

## iv. የፖሊሲ አስተምህሮ፣ ምርምር አጋርነት እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ

ይህ ዘርፍ በክልል ደረጃ ከፖሊሲ ጋር በተያያዘ ጥናትና ምርምር ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን መለየት፣ በስራ ላይ እንዲውሉ

የተደረጉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና አሰራሮችን አተገባበር በመዳሰስ የጥናት ርዕሰ ጉዳዮችን መለየት፣ ከመንግስት ተቋማት ጋር የተያያዙ አዳዲስ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና አሰራሮችን ማጥናት የሚያስችል የጥናት ርዕሰ ጉዳዮችን ማቅረብ፣

የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን በማከናወን አዳዲስ እውቀቶችን ለማመንጨት እና በሥራ ላይ ያሉትን ፖሊሲዎችንና አሰራሮችን ለማጠናከርና ለማሻሻል የሚያስችሉ ችግር ፈቺ የፖሊሲ ምክረ ሃሳቦችን ማፍለቅ፣ ጠቃሚ የሆኑ የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ መቀመር፣ ሳይንሳዊ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር መጽሔት ዝግጅት ላይ መሳተፍ፣ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፣ የዘርፉን የጥናትና ምርምር የክትትልና ድጋፍ ሥራዎችን ማከናወን። የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ውጤቶችን ተደራሽ ማድረግ፣ ክልላዊ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር አቅም መገንባት እና የመልካም ገጽታ ግንባታ ሥራ የሚያከናውን ነው።

ዘርፉ የተሰጠውን ተግባር በቅልጥፍናና በውጤታማነት ለማከናወን ያስችለው ዘንድ በሁለት ቡድኖች እንዲደራጅ መዋቅር ተበጅቶለታል። እያንዳንዱ ቡድን ደግሞ በስሩ ቡድን መሪ እና የተለያዩ ባለሙያዎች መደብ ተቀርጾለታል። የዚህ ዘርፍ ቡድኖች የሚከተሉት ናቸው፡-

i. የፖሊሲ አስተምህሮ እና የምርምር አጋርነት ቡድን
ii. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና የመረጃ ማዕከል ቡድን

# 3 በኢንስቲትዩቱ የተለያዩ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ዘርፎች የተከናወኑና እየተከናወኑ ያሉ የምርምር ስራዎች፤

## I. የተጠናቀቁ የጥናትና ምርምር ስራዎች

- በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የቁጠባ እና የኢንቨስትመንት ባህሪይ እና ጥንካሬ ወሳኞች ጥናት
- በማዕከለዊ ኢትዮጵያ ክልል የሴቶች ፖለቲካዊ ተሳትፎ ዕድሎችና ችግሮች ጥናት
- በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የአነስተኛ፣ ጥቃቅን፤ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች አፈጻጸም ጥናት
- በክልሉ ሰላምና መረጋጋትን የሚጎዱ ማነቆዎች መፍቻ የፖሊሲ አማራጭ ሀሳብ ጥናትና

## II. በሂደት ላይ ያሉ የጥናትና ምርምር ስራዎች

- የሴቶች ልማት ማህበር በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ያለው ተሳትፎ ደረጃ እድሎች እና ተግዳሮቶቹ ጥናት.
- በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የቱሪዝም እና የእደ ጥበብ ኢንዱስትሪ አቅም ለስራ እድል ፈጠራ ጥናት
- በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የባህላዊ ፍርድ ቤት አመሰራረትና አደረጃጀት ጥናት
- የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ህዝቦች የጋራ እሴቶች ጥናት
- የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የመልማት አቅምና ዕምቅ ሀብት ጥናት

# “ነገን ለመገንባት፤ ትላንትን ማጥናት!”

# “Researching the Past, Building the Future!”